# መ ቅ ድ ም

የየሃገሩ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባዎች /ሪፖርቶች/

የሰብአዊ መብት የየሃገሩ ሪፖርቶች (2006) በዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና በሠራተኛ ቢሮ የወጣ ማርች 6/2007 በዓለም ዙሪያ የተሻለ የግለሰብና የፖለቲካ ነፃነት እንዲሰፍን ሰዎች ጠንካራ ግፊት እያደረጉ ነው ። ለዴሞክራሲ ስርዓት አራማጅ ተቋማት መኖርም ትግል እያደረጉ ነው ። ፕሬዚዳንት ቡሽ "ለድርድር የማይቀርቡ የሰው ልጆች የክብር ጥያቄዎች"ሲሉ የጠሯቸውን ጉዳዮች ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ ።

በራስ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችና ሊያጋጥሙ የሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢኖሩም አንዳንድ ብርቱ ግለሰቦችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ቡድኖች ሰብአዊ መብቶችን የሚፃረሩ ድርጊቶችን አጋልጠዋል። እነዚህ ወገኖች አናሣ የጐሣና ኃይማኖት ተከታዮችን መብቶች ያስጠብቃሉ ። እንዲሁም የሰራተኞችንና የሴቶችን መብቶች ከማስጠበቅ በተጨማሪ ለኤኮኖሚ ጥቅም ማግኛ ሲባል ሰዎችን የማዘዋወርን እኩይ ተግባር ለማስቆም ጥረት ያደርጋሉ ። ጠንካራና ቀልጣፋ የሲቪል ማኅበረሰብ ለመገንባት፣ ነፃና ትክክለኛ ምርጫዎች እንዲካሄዱ ለማድረግና ሕግን መሠረት ያደረገ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ተጠያቂነት መኖሩ እንዲታወቅ ለማድረግ ይሰራሉ ። እነዚህ ለለውጥ የሚጓጉ አርበኞች የቀድሞውን ገደብ ሁሉ እየጣሱ በአዳዲስ ብይን እየለወጡት ይገኛሉ። በጥቂት ትውልዶች የሕልውና ዘመን በታደገው ዓለም የነፃነት መንፈስ ተስፋፍቷል ። የኮሚኒስቶች አምባገነንነት ጉራ ተደረማምሷል፣ ብሉም አዳዲስ የዴሞክራሲ ጉራዎች ነፍስ ዘርተዋል።በአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ የተቀረፁት መብቶች፣ በየሃገራቱ ከበፊቱ የበለጠ የሕግ ከለላ አግኝተዋል።

ይህ ምስጉንና ድንቅ ሥራ ይቀጥላል። ቁርጠኛ ተቀናቃኞች ስላሉበት ሥራው ተጠናቆ ፍፃሜ አግኝቷል ማለት ግን አይቻልም ። የዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚያስፈራቸው ወገኖች የለውጥ ሐዋርያትን ቢቃወሙ አያስገርምም። ባለፈው ዓመት ውስጥ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችንና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አቀንቃኞችን መውጪያ መግቢያ ለማሣጣትና ለማስፈራራት ወይም የሚያራምዷቸውን ሥራዎች ለመገደብ ወይም ለማስቆም የተደረጉ ሙከራዎችን እይተናል ። ነፃ አመለካከት የሚያራምዱ ወገኖችን ለመቃወም ፍትሕ የማያሰፍኑ ሕጎች እንደ ፖለቲካ መሣሪያ እንዲያገለግሉ ተደርጓል ። ተቃዋሚ /ተቃራኒ/ ድምፆችን ዝም ለማሰኘት ሕጋዊ ያልሆኑ ዘዴዎችን ሥራ ላይ የማዋል ሙከራዎች አይተናል ።

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የጅምላ ጥቃት ሲደርስባቸው ነፃነትና ዴሞክራሲ ቀስ በቀስ እየተዳከሙ ይሄዳሉ ። የዓለም ዴሞክራሲ ኃይሎች የሰብአዊ መብት፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጠበቆችን ጥበቃ ሊያደርጉላቸው ይገባል።ይህ ከወቅቱ ዲፕሎማሲያችን አቢይ ተልዕኮዎች አንደኛው ነው ። በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴራችን የወጡት የ2006 የየአገሩ ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሪፖርቶች በዚህ ረገድ የምናደርገውን ጥረት ወደፊት እንዲራመድ ይረዳሉ ። በነዚህ አሳቦች መደምደሚያነት እነሆ እነዚህን ሪፖርቶች *ለዩናይትድ ስቴትስ* ኮንግሬስ አቀርባለሁ ።

*ኮንዶሊዛ ራይስ*
*የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር*

## መ ግ ቢ ያ ፡-

የሰብዓዊ መብቶች ትግበራን በተመለከተ የየሃገራቱ ዘገባዎች -2006 በዴሞክራሲ፤ ሰብአዊ መብቶችና ሠራተኞች ቢሮ የወጣ መግለጫ፣ ማርች 6/2006፤

መንግስታት ሠብአዊ መብቶችን በሥራ ለመተርጐም የገቡአቸውን ዓለምአቀፍ ግዴታዎች በምን ያህል አጥጋቢ ሁኔታ ለመፈፀም እንደቻሉ እነዚህ ዘገባዎች ይገልፃሉ። እነዚህ በተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ የታቀፉ የሰው ልጅ መሠረታዊ መብቶች ጥያቄዎችን ኘሬዚደንት ቡሽ "ለድርድር የማይቀርቡ የሰው ልጆች የክብር መገለጫ ናቸው" ሲሉ የገለጿቸው ናቸው። የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ እንዳሉት "እነዚህ ዓለም አቀፍ የሰባዊ መብት ድንጋጌዎች ባንድ ሌሊት ዕውን የሚሆኑ አይደሉም። ይሁን እንጂ ይዋሉ ይደሩ የሚባሉ ደግሞ አይደሉም።"

እያንዳንዱ ግለሰብና በህብረተሰብ ውስጥ የሚንቀሳቀስ እያንዳንዱ ድርጅት የእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ተቀባይነትና ተፈፃሚነት እያደገ እንዲመጣ ባልተቋረጠ ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ የማስከበሪያ እርምጃዎች አማካይነት ዓለም አቀፋዊ ዕውቅናቸውና ተከባሪነታቸው እንዲረጋገጥ ዓለማቀፋዊው ድንጋጌ ጥሪ ያደርጋል። ***የዩናትድ ስቴትስ መንግስት*** ሰብአዊ መብቶች ለማክበር የገባቸውን ግዴታዎች በጥብቅ ያከብራል። ይህን ሪፖርት የምንጽፈው ለአሸባሪዎች ጥቃት በተጋለጥንበትና ደህንነታችንን ለማስጠበቅ ስንል አፀፋዊ ርምጃ በመውሰድ ላይ በምንገኝበት ወቅትና ሰብአዊ መብቶች የማስከበር መልካም ስማችን ጥያቄ ውስጥ በገባበት ጊዜ መሆኑን እንገነዘባለን። ***የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት*** በየጊዜው በሚያቀርባቸው ሪፖርቶች አማካይነት ሌሎች በእኛ ላይ ያላቸውን የሰብዓዊ መብት የማስከበር ጠንካራ እምነት እንዲጐለብት አበክረን እንሰራለን። ይህ ተግባራችን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የፈረምናቸው ግዴታዎች አንድ አካል እንደሆነ አድርገን እንቆጥራለን። ተከታታይነት ያለው መሻሻል እንዲመጣ በቁርጥኝነት ለመሥራት ቃል ገብተናል። ***የዩናትድ ስቴትስ*** ሕጐች፤ ፖሊሲዎችና ተጠርጣሪ ሽብርተኞችን የማገት፤ በዕግት በሚቆዩበት ጊዜ ስለሚደረግላቸው አያያዝና ጉዳያቸው በፍርድቤት ስለሚታይበት ሁኔታ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ መሻሻል ተደርጓል። የመንግስታችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንከን የለሽ ነው ማለት አይቻልም፣ ተጠያቂነት ግን አለበት። ጤናማውና ጠንካራው ሲቪል ማህበረሰባችን ፤ጉልበታሙ፣ ባለ ብዙ ሽፋኑና ትግርምት ፈጣሪው መገናኛ ብዙሀናችን፤ በነፃነት የሚሰሩት የመንግስታችን ዘርፎችና በጽኑ መሠረት ላይ የቆመው የሕግ ልእልና ስርዓታችን የማስተካከል ኃይል አላቸው ። እነዚህ ከዚህ በታች የቀረቡት የየሃገሩ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባዎች /ሪፖርቶች/ የኮንግሬስ ውክልና ያላቸው ሲሆን በመላው ዓለም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ***የዩናትድ ስቴትስ*** መንግስት ከሚያደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ አንደኛው ተግባር ነው። እነዚህ ዓመታዊ ሪፖርቶች ለሶስት አሰርታት በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገራት በሰብአዊ መብቶች ረገድ በተገኙ ድሎችም ሆነ ገና ባልተከናወኑ ተግባራት ላይ በተደረጉ የግምገማ ጥናቶች ውስጥ እንደማጣቀሻ ሰነዶች እየተወሰዱ ሲሰራባቸው ቆይቶአል። መንግስታትና ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን እንዳይረገጡ፣ ብሎም ሃገሮች ሁሉ መሰረታዊ መብቶችን የማስከበር አቅማቸው እንዲጐለብት የድርጊት ትብብር መሰረት ሆነው አገልግለዋል።

ሪፖርቶቹ በ2006 የነበሩትን የየሃገራቱን የሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ክንውን ይዳስሳሉ። እያንዳንዱ ሪፖርት ማጣቀሻ ሳያስፈልገው በራሱ ሙሉእ ነው። ይሁን እንጂ በደምሳሳው የሚመሳሰሉ ሁኔታዎች ይታያሉ።